# የካምፓስአዙል የደህንነት ጥበቃ

ካምፓስ አዙል ለሁሉም አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መፍጠር ይፈልጋል። ለዚያም ነው ካምፓስ አዙል የደህንነት ጽንሰ -ሐሳብን
ተግባራዊ የሚያደርገው ። ይህየደህንነት ጽንሰ -ሐሳብ በድርጅቱ ውስጥ ምቾት በማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ ቢገኙ ወይም ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ያብራራል። በዚህ መንገድ በካምፓስ አዙል የራሱን እሴቶች ያከብራል።

## 1 ቅሬታ ካለዎት የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ-

እርስዎ በክበብ ወይም በድርጅት ውስጥ ተሳታፊ ኖት? ወይም በካምፓስ አዙል ውስጥ በማገል ገል ላይ ይ ገኛሉ? ምቾት የማይ ሰጥ ነገር አጋጥሞት ያውቃል? ወይም የሚረብሾት ነገር አለ? እንግዲያውስ ቅሬታዎን በሚከተሉት አማራጮች ማቅረብ ይችላሉ።

- ለእምባ ጠባቂዎቻችን በኢሜል ይላኩ (ombudsteam@campus-asyl.de)
  የሕዝብ እንባ ጠባቂ የማያዳላ ነው። ይህም ማለት ቅሬታዎን ገለልተኛ ግለሰቦች በተጨባጭ ያዩታል ማለት ነው ።

**የሕዝብ እንባ ጠባቂዎች**

| | |
|---|---|
| Elisabeth Bauermann | elisabeth.bauermann@campus-asyl.de |
| Maen Soufan | maen.soufan@campus-asyl.de |
| Gabi Eisert | gabi.eisert@campus-asyl.de |

- ወደ ካምፓስ አዙል ጽሕፈት ቤት ወይም ለሕዝብ እንባ ጠባቂዎች በፖስታ በመላክ።
  አድራሻ: Bajuwarenstr. 1a፣ 93053 ሬገንስበርግ ፣ ጀርመን
- በፅሁፍ Zeißstr 9 ፣ 93053 ሬገንስበርግ በሚገኘው የመልዕክት ሳጥናችን ውስጥ በማስቀመጥ።
- በአካል ቢሮው ድረስ በመገኘት እና ስልክ በመደወል 0941 56803419

ቅሬታዎ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ተጽፎ ሊቀርብ ይችላል። ከዚያ ጽሑፉን ተርጉመን የምናቀርብ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አስተርጓሚ ሊዘጋጅ ይችላል።

## 2 ቅሬታ የሚስተናገደው በሚከተለው መንገድ ነው

እያንዳንዱ ቅሬታ በሕዝብ እንባ ጠባቂዎች በቡድን ይስተናገዳል።
የእንባ ጠባቂዎች ቅሬታዎን ሲቀበሉ ወዲያውኑ ያሳውቁዎትና ቀጣዮቹ ሂደቶች ምንምን እንደሆኑ ይነግሩዎታል።
የሕዝብ እንባ ጠባቂዎች እንደ ቦርዱ ፣ የአማካሪ ቦርድ ወይም ጽሕፈት ቤቱን የመሳሰሉ ሌሎች ሰዎችን ለማሳተፍ በጋራ ይወስናሉ። በተቻለ መጠን መረጃዎ/ ቅሬታዎ ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዲያውቁት የሚደረግ ሲሆን መረጃዎም ስም አልባ ሆኖ ይቆያል።

ከዚያ በኋላ እንባ ጠባቂዎች በሚከተለው መንገድ ይቀጥላሉ-

- እርስዎ ቅሬታዎትን ከሚሚያዩት ሰዎች ጋር ውይይት የሚያደርጉ ሲሆን በውይይቱ ወቅት ሁኔታዎን ግልጽ ለማድረግ ይሞክሩ::
- አስፈላጊ ከሆነ የልዩ ባለሙያ ኤጀንሲን ወይም የወጣቶች ደህንነት ቢሮን ማነጋገርም ይችላሉ።
- የፖሊስ ሪፖርት ማቅረብ ከፈለጉም ሊያግዙት ይችላሉ።